**የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምላሽ አሰጣጥን (የኮቪድ-19) አስመልክቶ የተዘጋጀ**
**ዕለታዊ መግለጫ**

በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ 164 የላብራቶሪ ምርመራ የተደረገ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አንድ (1) ሰው በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል። በቫይረሱ መያዛቸው የተረጋገጡት ግለሰብ የ 65 ዓመት ሴት በኦሮሚያ ክልል የዱከም ከተማ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ የውጭ ሀገር የጉዞ ታሪክ የሌላቸውና በቫይረሱ መያዙ ከተረጋገጠ ሰው ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑ አልተረጋገጠም። ታማሚዋ በሌላ ተጓዳኝ በሽታ ምክንያት በሆስፒታል ገብተው የነበረ ሰሆን በተጨማሪም የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምልክት በማሳየታቸው በተደረገላቸው የላብራቶሪ ምርመራ በኮሮና ቫይረስ የተያዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። በአሁኑ ሰዓት ታማሚዋ በለይቶ ማከሚያ በጽኑ ህሙማን ህክምና ክፍል ክትትል እየተደረገላቸው ሲሆን ከእርሳቸው ጋር የቅርብ ንክኪ የነበራቸው ሰዎች የመለየትና ክትትል ሂደት እየተከናወነ ይገኛል።

ይህ መረጃ እስከ ተደራጀበት ሰዓት ድረስ በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 2007 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 164 (139 ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ 26 በቫይረሱ ከተያዙ ሰዎች ጋር ንክክ የነበራቸው እንዲሁም የበሽታው ምልክት ያሳዩ ሰዎች) |
| በዛሬው እለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 1 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 36 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 1 |
| ያገገሙ | 4 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 2 |
| እስካ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 44 |

ህብረተሰቡ የበሽታውን ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት፡

- በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች በአፋጣኝ በ8335 ወይም 952 በመደወል ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት እንዲያሳውቁ፣
- ለተለያዩ ጉዳዮች በአንድ ቦታ መሰባሰብ በማስወገድ፣ እጅን አዘውትሮ በሳሙናና በውሀ በመታጠብ፣ በአካል ንክኪ የሚደረግ ሰላምታን በመተውና አካላዊ መራራቅን ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንዲከላከል እናሳስባለን።

ለተጨማሪ መረጃ በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ማግኘት ይቻላል፡

ዶ/ር ሊያ ታደሰ

የጤና ሚኒስትር

መጋቢት 28 ፣ 2012 ዓ.ም